ቁጥር ፬ - ሚያዝያ ፪ሺህ ፪ ዓመተ ምሕረት April 2010



ባለፈው ወር ውስጥ ከሦስት ዓመታት በፊት ያነበብኩትን ስለ ፈውስ የተጻፈ አንድ መጽሐፍ እና ስለ በሽታና ፈውስ የተጻፈ ሌላ መጽሐፍ አከታትዬ አነበብኩ። የዚህ መጣጥፍ መነሻ በመሆን ልጽፍ ያነሳሳኝና ከሁለቱ መጻሕፍት አንዱ የፈውስ ኪዳን የተሰኘው በሰይፉ ከበደ በ2003 (1996) የተጻፈው ነው። መጽሐፉ በርካታ ጠቃሚ ነጥቦችን የያዘ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችንም የጨበጠ ነው። ለምሳሌ፥ ክርስቲያኖች ሊታመሙ እንደሚችሉ፥ በሐኪሞች መፈወስ እንደሚቻል፥ የተጸለየለት ሁሉ እንደማይፈወስና ሊሞትም እንደሚችል፥ ወዘተ ሲገኙበት በሌላ ገጽታው ግን በመጽሐፉ ውስጥ ሁለት ዓይነት ግጭቶች አይቼበታለሁ።

በእውነተኛ የፈውስ ስጦታና በዘመኑ የፈውስ አገልግሎቶች መካከልና ዙሪያም የሚደረጉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ትምህርቶችና ልምምዶች በዝተው እየታዩ ናቸው። እውነተኛ የፈውስ ጸጋ ያላቸው ሰዎች ጌታ ራሱ እንዳገለገለ ወይም ቀድሞ ነቢያቱ ኋላም ሐዋርያቱ እንዳደረጉ እንዲያደርግ ፈር ተተልሞለታል። የፈውስ ስጦታ ያላቸው የሚመስላቸው ፈውሰኞች ደግሞ የመላና የነሲብ ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ።

በመጽሐፉ ውስጥ ካየኋቸው ግጭቶች አንዱ ዓይነት ከነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት እውነት የሆኑ አሳቦች ጋር የሚጋጩ አሳቦችም አብረው መስፈራቸው ነው። በአንዱ ክፍልና ምዕራፍ የተወሳው በሌላ ቦታ ከተጻፈው ጋር ካልተስማማ የእርስ በርስ ግጭቶች አሉበት ማለት ነው። ሁለተኛው በመጽሐፉ ውስጥ የተወሱት አንዳንድ አሳቦች ከጠቅላላው የመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ጋር ያላቸው ግጭት ነው። አንድ ትምህርት ወይም ልምምድ ከቃሉ ጋር ከተጋጨ ደግሞ ክፉ ነው። እነዚህ ትምህርቶችና ልምምዶች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በጣም ተንጸባርቀው ስላየሁ እነዚህን የመጽሐፉን አንቀጾች መንደርደሪያ በማድረግ የመጽሐፉን እይታና አጠቃላዩን የዘመኑን “የፈውሰኞች አገልግሎት” ልቃኝ እሞክራለሁ። በመጽሐፉ ውስጥ የተንጸባረቁት ትምህርቶች ፈውሰኞች እጅግ የሚጠቀሙባቸው ሐረጎችና ልምምዶች ናቸው። ስለዚህ ነው መጽሐፉንም ልምምዶቹንም ለመቃኘት የሞከርኩት።

መጽሐፍ ቅዱሳቸውን የማያጠኑና የሚነገራቸውን ሁሉ ያለጥያቄ የሚቀበሉ አማኞች ደግሞ በቀላሉ በመወናበድ የአካል ፈውስ ሳይኖር ሕመሙን መካድና በእምነት ግንባታ ፈንታም የእምነት መፍረስ እየተከተለባቸው ከመጣ ይህ ወገን እውነቱን እንዲያውቅና “እውነት መጽሐፍ ቅዱስ፥ ሙሉው የቃሉ ትምህርት ምን ይላል?” ብሎ እንዲጠይቅ ማበረታታት የአገልጋዮች ሁሉ ኃላፊነት ነው። በአብዛኛው ክርስቲያኑ ማኅበረ ሰብ፥ በተለይም “ጴንጤው” በቀላሉ አማኝና ከተጻፈው እውነት ይልቅ በስሜት ህዋሳት በሚሞከረው ልምምድ የሚደገፍ ነው። ሰባኪዎችንም አግዝፎ በሚያሳይ መነጽር ስለሚያይ እነዚህ ሰዎች የሚሳሳቱ አይመስሉትም። የሚናገሩትንና የሚያደርጉትንም በጅምላ መቀበል ብቻ እንጂ ለመመርመር አይሞክርም። የማይሞክረው ደግሞ በሚያምናቸው ሰዎች የሚሰበከውን ሁሉ በቀላሉ የሚያምን ስለሆነና ቃሉንም በስልት ስለማያጠና ነው።

## የመጽሐፉ ጭብጥ - የፈውስ መብት

ከመጽሐፉ ጭብጥ በፊት ከሽፋኑና ከርእሱ ልጀምር። ርእሱ (የፈውስ ኪዳን) ፈውስ ኪዳን ወይም ቃል ኪዳን መሆኑን ያመለክታል። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ስነ መለኮት ቃል ኪዳን በሁለት ወገኖች መካከል የሚገባ ቃል ነው። ይህ ኪዳን በሁለት እኩያዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ሳይሆን በኃያልና በታናሽ ወይም ደካማ ወገን መካከል የሚገባ ቃል ነው። ርእሱ መስህብነት ሊኖረው ይችላል። ሆኖም እኛ በአዲሱ ኪዳን ውስጥ የምንገኝ አማኞች መሆናችንን ሳንዘነጋ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ በሁለት ወገኖች መካከል የተገባ “የፈውስ ኪዳን” ተብሎ የተጠራ ኪዳን አለመኖሩን ማወቅ አለብን።

ወደ ጭብጡ ስንመጣ ደግሞ የመጽሐፉ ዋና አሳብና የጸሐፊው ጸሎት ሆኖ በመግቢያው የተጠቀሰው አንባቢዎች ወይም ክርስቲያኖች ከበሽታ መፈወስና በጤንነት መኖር መብታቸው እንደሆነ እንዲያውቁ ነው። በመግቢያው ገጽ የመጽሐፉ ዓላማ ሲዘረዝር፥

1. በበሽታ የሚማቅቁ ወገኖች በክርስቶስ የመገረፍ ቁስል እንደሚፈወሱ ለማሳወቅ
2. መለኮታዊ ጤንነት የልጆች መብት መሆኑን ለማስገንዘብ

ይልና አሁንም በዚያው በመግቢያው ገጽ፥

ይህን መጽሐፍ ስታነቡ ከማናችሁም በሽታ ለመፈወስ ብሎም በጤና ለመኖር መብታችሁ እንደሆነ እንድታውቁ ጸሎቴ ነው። . . . ይላል። በሌላ ገጽ፥

ሐኪም ይሁንላችሁ። ያለምንም ክፍያ «በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ» የተባለውን የፖሊሲ ቁጥር ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መቀበልና መፈወስ የልጅነት መብታችሁ መሆኑን አሳስባለሁ። አሜን!

መብት ማለት በቁሙ ይገባኛል የሚለው አሳብ ነው። ቃሉ በብሉይ ኪዳን ጥቂት ቦታዎች ተጠቅሶአል፤ ለምሳሌ፥ 2ሳሙ. 19፥28 እና ነህ. 2፥20። ቃሉ ጽዳቃህ ( הְקָדְצ ) የሚል ሆኖ ትርጉሙ ግብረ ገባዊ ሕይወትን በተመለከተ ጽድቅ ወይም ጻድቅ፥ ትክክል ወይም ልክ መሆን ማለት ነው። ቃሉ ዘፍ. 15፥6 ላይ ከተጻፈው አብራም በእግዚአብሔር አምኖ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት ከሚለው አንድ ነው። በአዲስ ኪዳን መብት የሚለው ቃል 8 ያህል ጊዜ ሲጻፍ ከዚህም አብዛኛው ተከማችቶ የሚገኘው በ1ቆሮ. 9 ነው። በዚህ ያለውም ሆነ በሌሎች ሁለት ጳውሎስ የጠቀሳቸው ስፍራዎች (1ቆሮ. 8፥9 እና ዕብ. 13፥10) ያለው ቃል አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ቋንቋ ሥልጣን ኤክሱሲያ (ἐξουσία) የተሰኘው ቃል ነው። ለምሳሌ በዮሐ. 1፥12 ለሚያምኑት ሁሉ የተሰጠውን ሥልጣን የሚለው ቃል ራሱ በሌላ ስፍራ መብት የተባለው ነው። ቃሉን በትንሹ ካየን አሳቡን እንቃኝ።

እግዚአብሔር በሽታ እንዳይነካን ሊጠብቀን የሚችልና ከነካንም ሊፈውሰን የሚችል ጌታ ነው። ይህ እውነት ነው። ይሁን እንጂ ፈውስና ጤንነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሥልጣንና መብት መሆናቸው አልተጠቀሰም። ይልቅስ ጤንነትና ፈውስ በዚህች በተረገመችና በወደቀች ምድር የእግዚአብሔር ጸጋ፥ በረከትና ምርቃት ናቸው። ፈውስና ጤንነት ከኖረን እያንዳንዲቱን ቀን ልንደሰትና ስለዚህም ልናመሰግን ይገባናል። መብትና ሥልጣን ናቸው ካልን ግን ይገቡኛል ልንል ነው። እነዚህ መብትና ሥልጣን የተባሉት ቃላት

ቁጥር ፬ - ሚያዝያ ፪ሺህ ፪ ዓመተ ምሕረት April 2010

ሕጋዊ ወይም ከሕግ ጋር የተቆራኙ ቃላት ቢሆኑም ለመረዳት ከእኛ የራቁ አይደሉም። በየቀኑ የምንለማመዳቸው ቃላት ናቸው።

በዓለማዊ ሥርዓት ሥልጣን የሚባለው ነገር ተዋረዳዊና ለሁሉም ያልሆነ ዕድል ነው። መብት ደግሞ ሰዎች ሊጠቀሙባቸውም ላይሠሩባቸውም የሚችሉ የዜጋ ሁሉ ሀብቶች ናቸው። ለምሳሌ እንደልብ መዘዋወር፥ አሳብንና እምነትን ሳይሳቀቁ መግለጥ፥ ርቱዕ ፍትሕ ማግኘት ወዘተ፥ መሠረታዊና ሁሉም የሚለማመዳቸው መብቶች ናቸው፤ እነዚህ ከሌሉ ኑሮና ዜግነት ጭንቅ ነው። አንዳንዱ መብት ከፈለግን የምናደርገው ካልፈለግን የማናደርገው፥ ለማድረግም ላለማድረግም የማንገደድበት ነው። ለምሳሌ፥ በምርጫ ጊዜ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ መብት ነው፤ ቢሆንም ይህንን ሁሉም ላያደርገው ይችላል። ባለማድረጉ ጉዳቱ ወዲያው ሊሰማውም ላይሰማውም ይችል ይሆናል። መሠረታዊ መብቶች ግን በየቀኑ የምንለማመዳቸው ናቸው። ወደ ክርስትና ከመጣንና ፈውስና ጤንነት መብት ነው የምንል ከሆነ እንደ መሠረታዊውና ዋናው መብት እናደርገዋለን እንጂ ካልፈለግን የምንተወው እንደማይደረግ እናምናለን፤ ምክንያቱም ጤንነትንና አለመታመምን የማይፈልግ ማንም የለምና። ስለዚህ አለመታመምና ከታመሙም ወዲያው መፈወስ ክርስቲያን ሁሉ በየቀኑ የሚለማመደው የየቀኑ ክስተት ወይም ዕለታዊ መብት ነው ብለን እንደመድማለን።

በዚህ ዘመን ጤንነትና ፈውስን ብቻ ሳይሆን ማናቸውንም ምድራዊ፥ ሥጋዊና ቁሳዊ ግብስብሶች ሁሉ ይገቡናል የሚሉ ክርስቲያኖችና አስተማሪዎች በብዙ ተባዝተዋል። ደግሞም ጤንነትና ፈውስ ማንም የሚፈልጋቸው ሸቀጦች ናቸው። እውነት ጤንነትና ፈውስ መብት ነው? በመጽሐፉ አገላለጥና በጸሐፊው እምነት መብት መሆኑ ከታች ከተወሰዱት ጥቅሶች ይታያል።

> በመለኮታዊ ፈውስ አምናለሁ! እልፎ ተርፎም በመለኮታዊ ጤንነት ለመኖር የተሰጠው ኪዳን ለእኛም ነው የሚል አቋም አለኝ። ኪዳኑም እንደዚህ የሚል ነው፣ *«አምላካችሁንም እግዚአብሔርን ታመልኩታላችሁ እርሱም እህልህንና ውኃህን ይባርካል በሽታንም ከመካከልህ አርቃለሁ። በምድርህም መካን ወይም የምትጨነግፍ አትሆንም፤ የዘመንህን ቁጥር እሞላዋለሁ (ዘጸ. 23:25-26)።* ይህ ኪዳን ከታመምን በኋላ ስለመፈወስ አይናገርም። በሽታ ከመምጣቱ በፊት ስላለን ጥበቃና በጤና

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኪዳናትና ተስፋዎች ይገኛሉ። ሁሉም ኪዳናትና ሁሉም ተስፋዎች የክርስቲያን ናቸው ማለት የዋኅነት ነው። አይደሉም። ለግለሰብ የተሰጠ ተስፋ አለ፤ ለአንድ ነገድ የተሰጠ ተስፋ አለ፤ ለእስራኤል እንደ ሕዝብ የተሰጠ ተስፋም አለ። ያን ሁሉ እንዳለ ቃል በቃል የኔ ነው፤ የኛ ነው ማለት ስሕተት ነው። ብሉይ ኪዳን አሮጌው ኪዳን ነው፤ ያ ኪዳን እንደ ኪዳን የተሰጠው ለአንድ ሕዝብ ነው። ያ ሕዝብም እስራኤል ነው። ያ ሕዝብ ትእዛዙን ቢጠብቅ በረከት ባይጠብቅ እርግማን ሊሆንበት ቃል የገባ ሕዝብ ነው። ቃሉን ጠብቆ ተባርኮአል፤ ሳይጠብቅ ቀርቶም መርገሙን ተቀብሎአል። ይህ መጽሐፍ ግን ያ ተስፋ ለአንድ ሕዝብ የተሰጠ አይደለም የሚል አቋም አለው። በመጽሐፉ ገጽ 168 እንዲህ ይላል፥

> **የፈውስ ኪዳን ለአንድ ለተለየ ሕዝብና ለተለየ ጊዜ ብቻ የተሰጠ እንዳልሆነ ለማገናዘብ እንደገና ዘጸ. 23:25-26 ድረስ አንብቦ ማሰላሰል ጠቃሚ ይሆናል።**

በክርስቶስ ደም በሆነው በአዲሱ ኪዳን ያለን አማኞች በሌላ ኪዳን ውስጥ የምንገኝ መሆናችንን ካላወቅንና አሮጌውንና አዲሱን ከቀየጥን ችግር ውስጥ እንገባለን። ያንን ኪዳን እንጠብቅ ብንልም መጠበቅ አንችልም። ጠብቀን እንድንባረክና ሳንጠብቅ ቀርተን እንድንረገም አይጠበቅብንም። ኪዳኑን እንጠብቅ ብንል እንኳ እንዲጠበቅ የሚደረጉት ነገሮች በአካል የሉም። ለምሳሌ መቅደስ የለም፤ አሮናዊ ሊቀ ክህነትና ሌዋዊ ክህነት ወዘተ የሉም። ከዚያ ኪዳን ደግሞ የማንፈልገውን እየጣልም የምንፈልገውን መርጠን እንድንወስድ አልተነገረንም። ለስሜታችን ደስ የሚለንን መርጠን እንውሰድ ብንል እንኳ የመምረጫው መለኪያ ምንድርነው? ስሜታችን ነው? እግዚአብሔር በሽታን ሊያርቅና ሕመምን ሊፈውስ የሚችል አምላክ ቢሆንም የብሉይን ተስፋዎች ሁሉ የኛ ተስፋዎች አድርገን እንዲህ ስላለ ይህ አይሆንብንም ማለት ወደ ስህተት ድምዳሜ ያደርሰናል። አሁንም በብሉይ ሕግ ስር የምንኖር ከሆንን ገና ከሕግ መርገም በታች ነን ማለት ነው። በደሙ የሆነው አዲስ ኪዳን ውስጥ አልገባንም ማለት ነው። በሁለት ኪዳናት ውስጥ መሆን ደግሞ አይቻልም። የሮሜ፥ የገላትያና የዕብራውያን መልእክቶች ጭብጦች ይህ የኪዳን መሻርና የኪዳን መቆም ነው።

ይህ መጽሐፍ የሕግን መርገም ኃጢአት፥ በሽታና ሞት ይላቸዋል።

> *ከሕግ እርግማን ዋጀን፣ የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ» ይላል (ገላ. 3:13-14)።* እርግማኖቹ ኃጢአት በሽታና ሞት ሲሆኑ የአብርሃም በረከት ደግሞ ፈውስንም እንደሚያካትት ጥያቄ አይኖረውም።

ኃጢአት በሽታና ሞት ከሕጉ መሰጠትና ከአሮጌው ኪዳን መቆም በፊትም እኮ ነበሩ። ሕጉ እነዚህንና ሌሎችንም ነገሮች አሳወቃቸው እንጂ አልጨመራቸውም። በሽታና ሞት የኃጢአት ውጤቶች መሆናቸው ከዘፍጥረት መጽሐፍ ይታያል። ጳውሎስ በገላትያ በግልጽ የሚያስተምረው ግን ስለ ኃጢአትና በሽታ ሳይሆን ስለ ሕግ ነው። እርግማኑ የሕግ እርግማን መሆኑንና የተዋጀነውም ከዚያ መሆኑን ነው የሚያብራራው።

ከፈውስ መብትነት አሳብ ሳንወጣ አንድ ሌላ ጥቅስ ልጨምር። በ3ዮሐ 2 የተጻፈው *ወዳጅ ሆይ፥ ነፍስህ እንደሚከናወን፥ በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ* የሚለው የሐዋርያው የዮሐንስ የሰላምታ ቃል የመለኮታዊ ጤንነትና የፈውስ ኪዳን እንደሆነ ተደርጎ በቃል-እምነትና አስተማሪዎችና በፈውሰኞች ይጠቀሳል። በዚህ መጽሐፍም ይህ ተጠቅሶአል፤

> **አምናለሁ። የእግዚአብሔር የቀድሞ አሳብ በሰጠው የፈውስ ኪዳን መሠረት በጤና እንድንኖር፣ ንብረታችን፣ ገንዘባችን፣ ከብቶቻችንና ቤተሰባችን እንዲፈወሱና ስኬታማዎች እንድንሆን ነው። እንዲያውም በእግዚአብሔር ቃል ላይ ሐዋርያው ዮሐንስ ለጋይዮስ በጻፈው ደብዳቤ ላይ *«ወዳጅ ሆይ ነፍስህ እንደሚከናወን በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ» ይላል (3ኛ ዮሐ. 2)።***

በመጀመሪያ ጋይዮስ በነፍስ የተከናወነ ሰው መሆኑን ቃሉ ስለሚነግረን ይህንን ሳናመነታ መቀበል አለብን። መንፈሳዊ መከናወን የሆነለት የተሳካለት፥ የተባረከ ሰው ነው። ከምንም ምድራዊና ቁሳዊና ሥጋዊ መከናወን ይህ እንደሚበልጥ ክርስቲያኖች ሁሉ የሚስማሙ ይመስለኛል። የማይስማሙ ሥጋውያን ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል።

ሁለተኛው ነጥብ ዮሐንስ እያደረገ ያለው ጸሎት ነው። ጤና እንዲኖረውና እንደ ነፍስ መከናወን ሁሉ በሌሎቹም ነገሮች መከናወንና መሳካት እንዲሆንለት እንደሚጸልይለት ነው የጻፈለት። ከአሳቡ በጥቅሉ ስንረዳ ምናልባት ጤናው ሙሉ ያልሆነ ሰው ይመስላል ጋይዮስ። ስለዚህ በመንፈሳዊ ሕይወቱ አንጻባራቂ ሕይወት እንዳለው ሁሉ እንደ መንፈሳዊው ስኬት በሥጋውም ጤና እንዲኖረውና በሌሎች ነገሮችም የተሳካለት እንዲሆን ለዚያም ይጸልይለታል። ጸሎት የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም ልመና ነው እንጂ የኪዳን አዋጅ አይደለም። የጸለይነው ሁሉ ይፈጸማል ማለት የዋኅነት ነው። የሚፈጸመው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ለዚህ ነው ልመናችንም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መሆን ያለበት። አንዳንድ ልመናዎቻችን የማይመለሱትም ስለዚህ ነው። ልመናዎቻችን ሁሉ ሙሉ በሙሉ እኛ እንደፈለግናቸው የተመለሱልን ቢሆን ኖሮ በተመለሱልን ልመናዎቻችን በራሳቸው ተውጠን በጠፋን ነበር! እግዚአብሔር ግን አዋቂ ነውና ፈቃዱን ይፈጽማል።

## የመገረፉ ቁስል ለጤንነት ወይስ ለደኅንነት?

ከመጽሐፉ ሽፋን ጀምሮ በውስጡ የናኘው በ1ጴጥ. 2፥24 ከተጻፈው ጥቅስ ወጥቶ የተወሰደ ሐረግ ነው። የመጽሐፉ 4ኛ እና 7ኛ ምእራፍም (ገጽ 65 እና 161) እንዲህ ተጠቅሶአል፥

> ይላል (ኢሳ 53:3):: አንዴ የተቀበለውንና የተሸከመውን በሽታችንን አንተው መልሰህ ተሸክም አይለንም:: በመስቀልም ላይ ሆኖ የተናገረው የመጨረሻው ቃል «ተፈጸመ» የሚል ነው (ዮሐ. 19:30):: ምንድነው የተፈጸመው? ድኅነትህ ተፈጽሟል፣ ፈውስህ ተፈጽሟል፣
>
> ይህ ቁስለኛ ነው እንግዲህ በአካል ላይና ውስጥ ካሉ ሕመምና ደዌ ሁሉ የሚፈውሰን:: ለበሽታ ሁሉ የኢየሱስ ቁስል ፍቱንና የማያዳግም መድኃኒት ነው:: ገዳይ ናቸው ለተባሉ በሽታዎችም እንኳ የፈውስ ኃይል ያለው በቁስሉ ውስጥ ነው:: ደሙ ኃጢአታችንን በሙሉ ሙልጭ አድርጐ እንደሚያጥብ ቁስሉ ደግሞ ከበሽታ አርነት ያወጣናል::

ደም ሳይፈስስ ስርየት እንደማይኖርና ቁስል ሳይኖር ደግሞ ደም እንደማይፈስስ እያስተዋልን ጥቅሱን በሙሉው እንየው። ቃሉ የሚለው *ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ* ነው። በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ የሚለው ሐረግ ነው በመጽሐፉ የተደጋገመው። ጥቅሱን በቦታውና ከጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ አንጻር ካየነው ስለ *ሥጋ* ፈውስ ሳይሆን ስለ ደኅንነት ነው የሚናገረው። እንዴት ቢባል ይህ ጥቅስ የጌታን *ሥጋ* መልበስ ዋና ምክንያት ነው የሚያመለክተው። ጌታ *ሥጋ* የለበሰበት ምክንያት አንዳንዶች በቁስሉ የመፈወስን ሐረግ ቆንጽለው እንደሚደግሙት ለ*ሥጋ* ፈውስ ሳይሆን ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ ወደ ነፍሳችን እረኛና ጠባቂ እንድንመለስ፥ ኃጢአታችንን በ*ሥጋው* ለመሸከም ነው። እንዴት ነው ለኃጢአት የምንሞተውና ለጽድቅ የምንኖረው? ጳውሎስ በሮሜ መልእክት እንደሚያብራራልን ከእርሱ ጋር በሞቱና በትንሣኤው በመመሳሰል ነው።

ጌታ በእንጨት ላይ ሲሰቀል የተሸከመው ደግሞ ሕመማችንን ሳይሆን ኃጢአታችንን ነው። የ*ሥጋ* ፈውስ የለም ማለት አይደለም። አለ። አንዳንዶች እንዲያውም ከወንጌሉ ይልቅ የ*ሥጋ* ፈውስና ተአምር እየፈለጉ ከእውነት እየሳቱ ይጠፋሉ። ይህ የፈውስ ቀውስ እየፈጠረ ነው። ሰዎች ሳይፈወሱ ተፈወሳችሁ እየተባሉ፥ ፈውስን ከጌታ ሳይሆን ከሰው እየተቀበሉ ሲከፍቱት ባዶ እየሆነባቸው፥ የ*ሥጋ* ፈውስን ብቻ እየፈለጉ ከ*ሥጋ* ፈውስ ያለፈውን ዘላለማዊውን የነፍስን ነገር እያጡ እየመጡ ናቸው። የ*ሥጋ* ፈውስ አለ። ሳንታመም መቅረታችን ወይም መኖራችን፥ በየቀኑ ከሕመምና ከአደጋ መጠበቃችን፥ በሕይወተ *ሥጋ* መኖራችን፥ ስንታመምም መፈወስና መዳናችን ይህ ሁሉ በጌታ የተደረገ ነው። ግን እነዚህ ነገሮች *ሥጋ* የመልበሱ ምክንያቶች አይደሉም። እነዚህን ነገሮች ለማድረግ ጌታ *ሥጋ* መልበስ አያስፈልገውም።

የ*ሥጋ* ፈውስ በረከቱና ምርቃቱ እንጂ የ*ሥጋ* መልበሱ ምክንያቱ አይደለም። እንዴት ቢባል ጥቂት ናሙና ምሳሌዎች እንይ፥

- ጌታ *ሥጋ* ሳይለብስ ሰዎች ተፈውሰዋል። ዘጸ. 15፥16 *እርሱም፦ አንተ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቀህ ብትሰማ፥ በፊቱም የሚበጀውን ብታደርግ፥ ትእዛዙንም ብታደምጥ፥ ሥርዓቱንም ሁሉ ብትጠብቅ፥ በግብፃውያን ላይ ያመጣሁትን በሽታ አላደርስብህም እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝና አለ ይላል።* ቀድሞም እግዚአብሔር ፈዋሽ እግዚአብሔር ነበር።
- *ቃልም ድርጊትም ሳይኖር ልመናና ጸሎትን ሰምቶ ፈውሶአል፤ ለምሳሌ፥ እግዚአብሔርም ሕዝቅያስን ሰማው፥ ሕዝቡንም ፈወሰ፤* 2ዜና. 30፥20።
- በመድኃኒትም ፈውሶአል፤ ለምሳሌ፥ 2ነገ. 20፥7 እና ኢሳ. 38፥21 ሕዝቅያስ በኢሳይያስ እንዴት እንደተፈወሰ ሲናገር፥ *ኢሳይስም፥ የበለስ ጥፍጥፍ አምጡልኝ አለ አምጥተውም በእባጩ ላይ አደረጉለት፥ እርሱም ተፈወሰ ይላል።*
- በተአምርም ፈውሶአል፤ ለምሳሌ፥ ኤልሳእ ንዕማንን ታጥቦ እንዲነጻ ነገረው ታጠበ ነጻ፤ 2ነገ. 5።

ይህ *ቃል ሥጋ* ሳይሆን በፊት ነው። እኛን፣ ማለትም፥ *ሥጋችንን* ከሕመምና ከደዌ ለመፈወስ ጌታ *ሥጋ* መልበስ አላስፈለገውም። የመስቀሉ ክቡር ገድል ለ*ሥጋችንም* ባርኮት መትረፉ እውነት ነው። ግን ጌታ *ሥጋ* ሳይለብስ ሰዎች በእጁም በቃሉም ተፈውሰዋል። *ሥጋ* ከለበሰም በኋላ ሳይገረፍ በፊት፥ በመስቀል ላይ ሳይውል በፊት ሰዎች ተፈውሰዋል። በወንጌላት የተጻፉትን ሌሎቹን ሁሉ ፈውሶች ትተን ከኢሳ. 53 ጥቅስ ጋር አብሮ የተጻፈውን ብንመለከት በማቴ. 8፥16-17 *በመሸም ጊዜ አጋንንት ያደረባቸውን ብዙዎችን ወደ እርሱ አመጡ፤ በነቢዩ በኢሳይያስ፥ እርሱ ድካማችንን ተቀበለ ደዌያችንንም ተሸከመ የተባለው ይፈጸም ዘንድ፥ መናፍስትን በቃሉ አወጣ፥ የታመሙትንም ሁሉ ፈወሰ* ተብሎ ተጽፎአል። ኢሳይያስ ይህን በሚናገርበት ጊዜ (ኢሳ. 53፥4) የተናገረው ስለ ጌታ የማዳን *ሥቃይ* ነው።

ማቴዎስ ይህን የጠቀሰው ደግሞ ገና ሳይሰቀል ስለፈጸመው ፈውስ ነው። ማቴዎስ እያሳየ ያለው ያ፥ በኢሳይያስ የተጠቀሰው የድካም ተቀባይና የደዌ ተሸካሚ ጌታ እርሱ መሆኑን ነው። ፈውስ በመገረፉ ቢሆን ኖሮ ከመገረፉ በፊት ፈውስ ባልኖረም ነበር። ከመገረፉ በኋላ ደግሞ ፈውስ መብት ቢሆንና ፈውስ እንደ ወንዝ ውኃ የሚቀዳ ቢሆን ኖሮ በዘመናትም በዘመናችንም ክርስቲያኖች ከቶም ባልታመሙም ነበር። እንግዲህ *ሥጋ* መልበሱ ለ*ሥጋችን* ጤንነት ሳይሆን ለነፍሳችን መዳን ነው። *ሥጋችንን* ይፈውሳል ግን ለ*ሥጋችን* ፈውስ መሞትና መሰቃየት አልነበረበትም። ሳይሰቃይ ፈውሶአል፥ አድኖአል፥ ከሞትም አስነስቶአል። በመስቀል ላይ የዋለው ግን ስለ ኃጢአታችን ነው። ደሙ ለነፍሳችን፥ ቁስሉ ለ*ሥጋችን* አይደለም። የቆሰለው ደሙ እንዲፈስ ነው። ሳይገረፍና ሳይቸነከር ደሙ እንዴት እንዲፈስስ ነው

የሚጠበቀው? ግርፋቱም፥ የእሾህ አክሊሉም፥ ችንካሩም ኃጢአታችን የተሰረየበትና አዲሱ ኪዳን የቆመበት የደሙ መፍሰስ መሳሪያዎች ናቸው። መስቀሉን ከኃጢአታችን ስርየትና ከነፍሳችን ቤዛነት ላነሰ ነገር መለወጥ ቃሉን መሸቃቀጥ ነው። ወንጌሉን መቸርቸር ነው። ጴጥሮስ እንደሚያስተምረን ጌታ ሥጋ መልበሱ ለምሳሌያችን ብቻ ሳይሆን ከዚያም ላለፈ ነገር፥ ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ለመሸከም ነው።

## የበሽታ ምንጮችና የእግዚአብሔር ሚና

በመጽሐፉ በመጀመሪያው ምእራፍ የተጠቀሱት የበሽታ ምንጮች ሰይጣን፥ ኃጢአት፥ አደጋ፥ ሱስና ልማዶች፥ ጤናን አለመጠበቅና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እግዚአብሔር ናቸው። ከመጀመሪያዎቹ አምስት አንዱ በሌላው ውስጥ የመካተት ባህርይ ቢታይባቸውም ሁሉም ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። ላተኩር የምፈልገው ግን ስድስተኛው ምንጭ ላይ ነው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እግዚአብሔርም የበሽታ ምንጭ መሆኑ ተጠቅሶ የተሰጡት ምሳሌዎች በሙሉ ግን በሽታዎቹና መከራዎቹ ከእግዚአብሔር በሰዎቹ ላይ የደረሱት ለጥፋት ቅጣት ሆነው ነው። የዚህ ድምዳሜ ክርስቲያን [ማንም ሰው ሊሆንም ይችላል] ከታመመ በሽታው የበደል ቅጣት ሆኖ መምጣቱ ነው። ይህ አልፎ አልፎ ሊሆምን ይችላል። ነገር ግን ሁሌ ምክንያቱ ይህ ነው ከተባለ ጤናማዎች (ክርስቲያን ያልሆኑትም ጨምሮ) ያልበደሉ በሽተኞች ሁሉ የበደሉ ያስመስላል። ክርስቶስን የማያውቁ ጤናማ ሰዎች አሉ፤ ታማሚ የሆኑ ክርስቲያኖች ደግሞ አሉ። ኩነኔ የሌለባቸውን ክርስቲያኖች አደጋም ሱስም ሳይይዛቸው፥ ንጽሕናቸውም ሳይጎድል ቀርተው በሆነ ምክንያት ቢታመሙ በደለኞች ሆነው ሊወገዙ ነው። ፈውሰኞች ያለአንዳች ቅሬታና ርኅራኄ ከመድረኮቻቸው ላይ ይህንን ደጋግመው ሲናገሩ ይስተዋላል። ሕመም ከእግዚአብሔር ሊሆን እንደሚችል ሲጠቀስ ለቅጣት ብቻ እንደሆነ ይነገራል። ይህ ክርስቲያን ሕሙማንን ሁሉ የሚረብሽ ድምዳሜ ነው። ይህ አባባላቸው እውነት ያለመሆኑንም እናውቃለን።

እዚህ ላይ የተዘነጋው ወይም ያልተነሣው የእግዚአብሔር ፈቃድና ሉዓላዊነቱ ነው። የእግዚአብሔር አሳብና መልካም ፈቃዱ እንዲፈጸም ሕመም በክርስቲያኖች ላይ ሊመጣ መቻሉ መካድ የለበትም። እንደ ኢዮብ የመሰለ የተመሰገነና በእግዚአብሔር በራሱም የተመሰከረለት በደዌ የተመታ ቅንና ፍጹም ሰው የለም። ይህ ደዌና አደጋ ቅጣት አልነበረም። አንዳንድ ፈውሰኞች ኢዮብ 3፥25ን በመጥቀስ በኢዮብ ላይ መከራው ሁሉ የመጣበት በመተማመን ፈንታ ገና ለገና ይደርስብኛል ብሎ እየፈራ እየተሳቀቀ ይኖር ስለነበረ (negative confession ይሉታል) ነው ይላሉ። ይህ ስንደዶ መዝዞ ቤት መሥራት የሚመስል ስህተት ነው። አለመሆኑ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምእራፎች ግልጽ ነዋ!

ሐዋርያው ጳውሎስ የሥጋው መውጊያ የነበረው ሰው ነው (2ቆሮ. 12)። ይህ ሦስት ጊዜ ጸልዮ ያልተወሰደለት ነገር ምን መሆኑን አናውቅም ግን ሥጋውን የሚያደክም ነገር ነው። ለምን እንዳልተወሰደም አናውቅም። አንድ ነገር ግን እናውቃለን፤ ይህ ድካሙ የክርስቶስ ኃይል ያድርበት ዘንድ ምክንያት ሆኖ አስደስቶታል። ጳውሎስ ይህ የሆነበት የበደል ቅጣት ተደርጎ አለመሆኑን እናውቃለን።

ከጳውሎስ ጋር ሲያገለግሉ ከነበሩት መካከል ጥሮፊሞስ አንዱ ነው። *ጥሮፊሞስን ግን ታሞ በሚሊጢን ተውሁት* አለ 2ጢሞ. 4፥20። ይህ መልእክት የተጻፈለት ጢሞቴዎስ ራሱ የሆድ ሕመምና የበሽታ ብዛት የነበረበት አገልጋይ ነበረ። 1ጢሞ. 5፥27 *ስለ ሆድህና ስለ በሽታህ ብዛት ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ፥ ወደ ፊት ውኃ ብቻ አትጠጣ* ብሎታል። አፍሮዲጡ ደግሞ ከፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የተላከ ከጳውሎስ ጋር ያገለገለ ወንድም ነው። ይህም ሰው ታምሞ ነበር፤ ለፊልጵስዩስ ምእመናን ሲጽፍ፥ *ሁላችሁን ይናፍቃልና፥ እንደ ታመመም ስለ ሰማችሁ ይተክዛል። በእውነት ታሞ ለሞት እንኳ ቀርቦ ነበርና፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ማረው፥ ኀዘን በኀዘን ላይ እንዳይጨመርብኝ ለእኔ ደግሞ እንጂ ለእርሱ ብቻ አይደለም።* (ፊል. 2፥26-27) እንዲህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጌታ ፈቃድ ውስጥ የተመላለሱ ነገር ግን የታመሙ ሰዎችን እናገኛለን። ይህ ሕመማቸው የበደላቸው ቅጣት ይሆን? ጳውሎስ ጸልዮላቸው የተፈወሱ ሰዎች መኖራቸው ተጽፎልናል። እነዚህ ለምን አልተፈወሱም? አናውቅም። ሳይጸልይላቸው ቀርቶ ብለን እንገምት ይሆናል፤ ግን የማይመስል ግምት ነው። አንድ ነገር ግን ግልጽ ነው፤ ጌታ እግዚአብሔር የወደደውንና የፈቀደውን ማድረግ የሚችል ማንም 'ምን ታደርጋለህ? ወይም ለምን ታደርጋለህ?' የማይለው ሉዓላዊ አምላክ ነው። እርሱ የወደደውንና ጠቃሚ መስሎ የታየውን ያደርጋል። ያ ስደታችንን፥ መከራችንንና ሕመማችንንም ይጨምራል። የዘመናችን ፈውሰኞች መታረቅ ያለባቸው ከዚህ ትልቅ እውነት ጋር ነው። ታማሚ የሆኑ ክርስቲያኖችም አሜን ማለት ያለባቸው ለዚህ ከኛ እውቀት ላለፈ ፈቃዱ ነው። በእርግጥ እግዚአብሔር የሚቀጣ አባት ቢሆንም ሕመም ሁሉ ቅጣት አይደለም። ልቡናችንም፥ መንፈስ ቅዱስም፥ ቃሉም ይህን ይመሰክሩልናል።

የመጽሐፉ ሁለተኛ ምእራፍ ርእስ ፈውስ የልጆች እንጀራ ነው የሚል ነው። "'ፈውስ የልጆች እንጀራ ነው' ተብሎ እንደተጻፈው" እስኪባል ድረስ ይህ ሐረግ የተለመደ ሆኖ በአገልጋዮችና በምእመናን አፍ ውስጥ ገብቶአል። 'ፈውስ የልጆች እንጀራ ነው' ተብሎ አልተጻፈም። አሳቡ በተወሰደበት ማቴ 15 እና ማር. 7 የተባለላት ሴት ግሪካዊት፥ ከነናዊት፥ ሲሮፊኒቃዊት መሆኗን ተነግሮአል። በተደጋገመ ቃል አይሁድ አለመሆኗ ነው የተወጋው። በጌታ ቃል ልጆች የተሰኙት አይሁድ ናቸው። በመጀመሪያ ሊያገለግል የመጣው እነርሱን ነበር። እኛ ራሳችንን ከሁለቱ ከአንዱ ጋር ማመሳሰል ከኖረብን ራሳችንን ማመሳሰል ያለብን ከአይሁድ ጋር ሳይሆን የአሕዛብ ወገን ከሆነችው ጋር ነው። ፈውስ የኛ እንጀራ ነው ማለት ያለባቸው አይሁድ ናቸው፤ እኛ ደግሞ አሕዛብ እንጂ አይሁድ አይደለንም። በእርግጥ በክርስቶስ በኩል፥ ማለትም እርሱን በመቀበላችንና በእርሱ በማመናችን ምክንያት የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል። እንግዲህ ፈውስ የኛ እንጀራ የተደረገው ለዚህ ይሆናል። ይህ ደግሞ ከላይ ከተወሳው መብት ወይም ሥልጣን ጋር ከተያያዘ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ በምናልፍበት ጎዳና ስናልፍ ሕመም ወይም መከራ ቢገጥመን አጉረምራሚ ክርስቲያኖች ሆነን ልንጓዝ ያደርገናል።

## የበሽታ ምልክቶች ይዋሻሉ?

"የበሽታ ምልክቶች ይዋሻሉ፤ ጌታ ግን አይዋሽም" የሚለው ሐረግ በመጽሐፉ በርካታ ገጾች ተደጋግሞ ይገኛል፤ ገጽ 33፥55፥78።

**ተቀበለ እንጂ /ማቴ. 8:10/:: እኛም ፈውሳችንን አምነን መቀበል ይጠበቅብናል:: የበሽታ ምልክቶች ይዋሻሉ፣ ጌታ ግን አይዋሽም:: ጌታ ፈወስሁ ካለ ፈወሰ ማለት ነው::**

**በእርሱ የፈውስ ኃይል ማመን የሚጠበቅብህ:: አዎን የበሽታ ምልክቶች ይዋሻሉ! እኔ ፈዋሽህ እግዝብሔር ነኝ ያለ አምላክ ግን አይዋሽም:: ሃሌ ሉያ!**

www.Ethiocross.com The Christian Voice,Beyond Church!



**የለምና:: የበሽታ ምልክቶች ይዋሻሉ ጌታ ግን አይዋሽም! ስለዚህ ምልክቶቹ የሚሉትን አትስማ ጌታ በቃሉ ሚናገርህን ስማ::**

ይህ በፈውሰኞችም የሚደጋገም ሐረግ ነው። በሽታ ከጠፋ የበሽታ ምልክቶች የሚኖሩበትና እየኖሩ የሚዋሹበት ምክንያት ግልጽ አይደለም። ፈውስ ከኖረ በሽታው የለም እኮ! በሽታው ከሌለ ምልክቶቹ ከየት መጡ? ምልክቶቹ ካሉ ፈውሱ የለም ወይም አልነበረም ማለት ነው። አንዳንድ ሕሙማን ለመፈወስ ከመጠን ያለፈ ከመጓጓታቸውና ከመጠበቃቸው የተነሣ (የስነ ልቡና ጠበብት ይህን ሁኔታ hypersuggestibility ይሉታል) በስሜታቸው ግለት ውስጥ ሆነው የተፈወሱ መስሎአቸው እንደተፈወሱ ይመሰክራሉ። የሚመሰክሩት ደግሞ መስሎአቸው ብቻ ሳይሆን ያልተፈወሱ ከሆነ መናገራቸው እምነታቸውን እንዲጨምርላቸውና ፈውሳቸው እንዲረጋገጥ እንዲናገሩ ስለሚገፋፉ ነው። ይህ ሰው ሠራሽና ዘመን አመጣሽ የፈውስ ሙከራ ዘዴ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን ፈውስ ሁሉ ግን እውነተኛና የማያዳግም ፈውስ ነው። ወይስ "የበሽታ ምልክቶች ይዋሻሉ" ሲባል በሽታውን እንደሌለ መቁጠርን የማበረታታት ትምህርት ይሆን? ጸሐፊው በትንሹም ቢሆን በሕክምና ሙያ ለብዙ ዘመናት ተሰማርተው ሠርተው እንደነበር በዚህም በሌላ መጽሐፋቸውም ጽፈው አንብቤአለሁ። የበሽታ ምልክቶች እንደማይዋሹ ሐኪሞች የማያስተምሩ ከሆነ፥ የእግዚአብሔርም ቃል የማያስተምር ከሆነ ይህ ትምህርት ከየት የተገኘ ይሆን?

በተለይ ተፈውሰው ወደ ሕመም የሚመለሱ ሰዎች ለምን ይህ እንደሚሆንባቸው በ6ኛው ምእራፍ የተገኘ ፈውስ ለምን ይጠፋል? በሚል ንዑስ ርእስ ስር የቀረቡት 4 ምክንያቶች ጥርጥር፥ ኃጢአት፥ የእምነት መጉደልና ፍርሃት ናቸው። እንደ ማስረጃ የተጠቀሰውም በዮሐ. 5 የተጻፈው 38 ዓመት ሽባ የነበረው ሰው ታሪክ ነው። *«ከዚህም በኋላ ኢየሱስ በመቅደስ አገኘውና እነሆ ድነሃል ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ወደፊት ኃጢአት አትስራ አለው» (ዮሐ. 5:14)::* **በዚህ ጥቅስ መሠረት ኃጢአት መሥራት በሽታን ይመልሳል ማለት ነው:: ስለሆነም ፈውስን ተቀብሎ ያለ ቅድስና መኖር አደገኛነት አለው::**

ፈውስን ተቀብሎም ሆነ ሳይቀበሉ ያለቅድስና መኖር አደገኝነት አለው። ይሁን እንጂ የተገኘ ፈውስ ሲጠፋና በሽታ ተመልሶ ወደ ተፈወሱ ሕሙማን ሲመጣ በወንጌላት ውስጥ አልታየም። በሐዋርያት አገልግሎትም አልታየም። ወይም እነዚያ የተፈወሱ ሰዎች ከቶም ኃጢአት አልሠሩም ማለት ነው። ደግሞም ያ የሆነባቸው በሽታ ኃጢአት ሠርተው የመጣባቸው ቅጣት ነው ልንል ነው። እንዲህ ካልን ስነ መለኮታችን ያዘመመ ይሆንብናል። ከዚህ የባሰ እና ከዚህ የከፋ የተባለው የከፋ በሽታን ሳይሆን የኃጢአት ውጤት የሆነውን ሞትና ያንን ተከትሎ የሚመጣ ቅጣት መሆኑ ከዐውዱ ይስተዋላል።

በዚህ ዘመን ግን ተፈወሱ ይባልና መነጽር ተሰብሮ፥ መድኃኒት ተበትኖ፥ የሐኪምና የሕክምና ቀጠሮ ተሰርዞ፥ ቀድሞም ያልጠፋው በሽታ ሲያይልና በመድኃኒት እየጠፋ የነበረውም ሲያገረሽ በሽተኞቹ በጠባሳቸው ላይ የኃጢአተኝነት ንቅሳት ተወቅረው ይኮማተራሉ። ፈውሰኞቹ ግን እንደ ሐውልት የቆመ ገናና ስም ይዘው ይዘልቃሉ። ይህን ያልኩት ሳይፈወሱ ተፈወሳችሁ የተባሉና የተሰቃዩ የሞቱም ብዙ ሰዎችን ስለማውቅ ነው። ቆም ብለን መጠየቅ የተገባን ነገር፥ ፈውስ ኖሮ ጠፋ ወይስ መጀመሪያውኑ ነበረም? ወይስ ፈውሱ የጊዜውና የጉባኤው የስሜት ሞቅታና ግርግር እንዲሁም ይሆናል ብሎ ከመጠበቅና አጥብቆ ከመጓጓት የተነሣ የተሰማ ስሜት ነው? ወይስ ፈውሰኞቹ የፈውስ ጸጋ የሌላቸው አስመሳዮች ናቸው? ብለን መሆን አለበት።

## ተፈጸመ ያለው ለበሽታና ችግር ነው?

ጌታ በመስቀል ላይ ሲውል ወደ መጨረሻ ላይ ከተናገራቸው ቃላት አንዱ ተፈጸመ የሚል ቃል ነው። በመጽሐፉ ገጽ 43-44 ላይ ጌታ ተፈጸመ ሲል የሆነው እንዲህ ተጽፎአል፤

> **ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመከራውም መጨረሻ ላይ *«ተፈጸመ»* አለ /ዮሐ. 19:30/:: ምንድነው የተፈጸመው? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ኃጢአታችን፣ በሽታችንና ሌሎችም ችግሮቻችን አበቃላቸው ማለት ነው::. . .**
>
> **ይላል (ኢሳ. 53:3):: እንዴ የተቀበለውንና የተሸከመውን በሽታችንን አንተው መልሰህ ተሸከም አይለንም:: በመስቀልም ላይ ሆኖ የተናገረው የመጨረሻው ቃል «ተፈጸመ» የሚል ነው (ዮሐ. 19:30):: ምንድነው የተፈጸመው? ድነትህ ተፈጽሟል፣ ፈውስህ ተፈጽሟል፣**

ይህ መጽሐፍ ከመስቀሉ ወዲህ ላለን አማኞች በሽታ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ችግሮቻችን ሁሉ እንደተወገዱ ያውጃል። ታዲያ ሕመምንም ጨምሮ በዘመናት በክርስቲያኖች ላይ የደረሰው ሕመምም ሆነ መከራ ሁሉ ለምን ሆነ? ፈውሰኞች ለዚህ መልስ አላቸው። ያም ካለማመናችን የተነሣ ነው ይሉና እምነትንም ሆነ ፈውስን ውስብስብና ረቂቅ ጽንሰ አሳብ በማድረግ የጥቂት ብቁዓን ንብረት ብቻ ያደርጉታል። የመጽሐፍ ቅዱስ ፈውስ ውስብስብ አልነበረም። በመስቀሉ ወደተፈጸመው እውነት ስንመጣ ግን የተፈጸመው በሽታና መከራ ሳይሆን የእግዚአብሔር የደኅንነት ሥራ ነው በመስቀሉ ላይ የተጠናቀቀው። ለመዳን ያንን ብቻ መቀበል እንጂ ከመስቀሉ ወዲህ የተደረገና እንዲደረግ የተጠየቀ ሌላ ነገር አልኖረም። የመስቀሉን ሥራ ያመነና ጌታን የተቀበለ ሁሉ መዳኑ የማያጠራጥርና የታተመ እንደሆነ ሁሉ ጤንነቱና ፈውሱም እንደ ደኅንነቱ ሁሉ ልክ ጌታን ሲቀበል የተጨበጠ መሆን ነበረበት። ግን አለመሆኑን ጸሐፊውም ካለፉበት ልምዳቸው ያውቁታል። ሁላችን ጌታን የምንከተልም እናውቃለን። ከሁላችንም ልምምድ በላይ ደግሞ ቅዱስ ቃሉ በግልጽ መዳናችንና የልጅነት ሥልጣናችን እውነት መሆኑን እንደሚናገር ጤንነትና ፈውሳችን በፖሊሲ ቁጥር ሙብት መሆኑን አልነገረንም።

> **ሐኪም ይሁንላችሁ:: ያለምንም ክፍያ «በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ» የተባለውን የፖሊሲ ቁጥር ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መቀበልና መፈወስ የልጅነት መብታችሁ መሆኑን አሳስባለሁ:: አሜን!**

መስቀሉን በመስቀሉ ላይ ከሆነው ላነሰና ለሌላ ነገር መለወጥ ያንን ድንቅ ሥራ ማራከስ ነው። አንድ ክርስቲያን መታመም ከቶም የለበትም ከሚል ሰው ጋር ስንነጋገር፥ "ከመስቀሉ ሥራ ኃጢአት መወገዱ እኮ አልተቀነሰም፤ የበሽታ መወገድ ተጨመረበት እንጂ" አለ። መቀነስም መጨመርን ማርከስ ነው። በግማሽ ብርጭቆ ወተት ላይ ወተቱን ሳንቀንስ ውኃ ብንጨምርበት አላቀጠንነውም? አላረከስነውም? ለምሳሌ በገጽ 86፥

በእንጨት ላይ የሚሰቀል ርጉም ይሁን ተብሎ እንደተጻፈ ክርስቶስ የእኛን የኀጢአትና የበሽታ ርግማን የጠረቀልን በመስቀል ላይ ነው /ገላ. 3:13-14/፡፡ የአብርሃም በረከት ተካፋዮች ስለሆንን ጤንነታችንም ሆነ ደኅንነታችን የመነጨው ከክርስቶስ መስቀል ነው፡፡

*ቃሉ የሚለው ግን፥ በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን* ነው። የሕግ እርግማንና የበሽታ እርግማን አንድ ከሆኑ ሕግ በሽታ፥ በሽታም ሕግ ነው ልንል ነው። አይደለም። ይህ በሕግና በጸጋ፥ በአሮጌውና በአዲሱ ኪዳን መካከል ያለውን ልዩነት ማደብዘዝ ብቻ ሳይሆን በላጺስ መደምሰስ ነው። ከመስቀሉ ወዲህ በተለያዩ ሕመሞች ያለፉትንና በማለፍ ላይ የሚገኙ ቅዱሳንን እምነት ማንኳሰስ ነው።

## እምነትና ፈውስ

እምነት ሲባል ፈውሰኞች በተለይ ፈውስን በተመለከተ ለእምነት የሚሰጡት ልዩ ትርጉም አለ። ያም ኃይል ነው፤ ፈውስን የሚያንቀሳቅስና እንዲከሰት የሚያደርግ ኃይል ይሉታል። በገጽ 95 እንዲህ ተጽፎአል፤

ሁሉ ነገር ይንተሳቀሳል፣ እንዲንተሳቀስም የሚያደረግ ኃይል አለው፡፡ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ፈውስንና ተአምራትን ሲያንቀሳቅስ የሚታየው በሰዎች ውስጥ ያለ እምነት ነው፡፡. . .

ይህ ወደ ተለመደው ያታከተ ድግግሞሽ፥ ማለትም፥ ያልተፈወሰው ሰው የታመመው እምነት ስላልነበረው፥ ያልተፈወሰውም እምነት ስለሌለው ነው ወደሚለው ድምዳሜያቸው ይመራናል። ፈውሰኞችና ዘመናዊዎቹ የቃል-እምነት አስተማሪዎች እምነትን ረቂቅና በራሱ ተአምራትን የማድረግ ኃይል ያለው ነው ብለው ያስተምራሉ።

እርግጥ ነው፤ ጌታ የሰዎችን እምነት ጠይቆአል። የጠየቃቸው እምነት ደግሞ ልቀቱን ወይም በእርሱ ማመናቸውን ነበር። ይህን ሳያደርግ፥ ማለትም እምነትን ሳይጠይቅም እኮ ፈውሶአል። ለምሳሌ፥ ዮሐ. 9 ውስጥ የተተረከው እውር ተፈውሶ ነው በኋላ፥ *አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን?* ተብሎ የተጠየቀው። ስለዚህ የሰዎች እምነት ቢኖርም ባይኖርም እርሱ ለመሥራት አልታገደም ወይም ሳይችል አልቀረም።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት በእግዚአብሔር መታመንና እርሱን መደገፍ ነው። እርሱ ደግሞ አምላክ ነውና የወደድነውን ሳይሆን የወደደውን ሊያደርግ ሥልጣን አለው። የወደደውን ቢያደርግም (ይህ ሕመምንና መከራንም ይጨምራል) ሳይናወጡ በእርሱ መታመንና እርሱን መደገፍ ነው።

እግዚአብሔር ሕይወታችን ልጁን ክርስቶስ ኢየሱስን እንዲመስል የሚያደርግ ማናቸውንም ነገር ወደ ሕይወታችን ሊያመጣ ይችላል። የሚመጣው ነገር ሁሉ ደግሞ በጎ ባይሆንም ውጤቱ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን፤ ሮሜ. 8፥28-29። ተግባራዊ በሆነ መልኩ እምነት ማለት አሜን ማለት ነው። አድራጊው እግዚአብሔር በሚያደርገው ነገር ተስማምቶ እሺ፥ ይሁን ማለት ነው። እምነትንም ሆነ ጸሎትን የእግዚአብሔርን እጅ መጠምዘዣ አድርገን ማየት የሥጋዊ ክርስቲያንነት ምልክት ነው። እነዚህን ነገሮች እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት መገንቢያ አድርጎ ይጠቀምባቸዋል እንጂ እርሱ እንዲሠራ እነዚህ ነገሮች ያስፈልጉታል፤ ወይም እነዚህ ነገሮች ከሌሉ እጁ እንደታሰረ ሰው ምንም ነገር ሊያደርግ አይችልም ማለት አይደለም። እምነታቸው እንደፈወሳቸው የተነገራቸው ሰዎች በጌታ ላይ ያላቸው እምነትና ከርሱ ጋር ያላቸው ግንኙነት ለውጥ ነው። እምነት ብቻውን የሚያድንም የሚፈውስም ጉልበት የለውም። ቢኖረውማ ኖሮ ጌታን እስኪያገኙት ድረስ መጠበቅ ለምን አስፈለገ? ቀድሞውኑ እምነታቸውን አንቀሳቅሰው መፈወስ አይችሉም ነበር? አዳኙ እምነቱ ሳይሆን እምነቱ የተጣለበት ጌታ መሆኑ ከዚህ ይታያል።

በመጽሐፉ ምእራፍ 6 የተጸለየላቸው ሁሉ እንደማይፈወሱ ምክንያት ከሚሆኑ ነጥቦች ጋር ተወስቶአል። የተጸለየላቸው ሁሉ አለመፈወሳቸው እውነት ነው። ከላይ የተጠቀሱት እነጳውሎስም አለመፈወሳቸው ተጠቅሶአል። ግጭቱ ግን ፈውስ የልጆች እንጀራና መለኮታዊ ኪዳን ሲሆንና እነዚህና ሌሎችም የማይፈወሱ ከሆነ ነው። ፈውስን የክርስቲያን የልጅነት መብት አድርገን ካስተማርንና ይህንን መብት መብቴ ብሎ እንዲቆም ከነገርነው ይህ ሰው ቢታመም ልጅነቱን እና እምነቱን ይጠራጠራል። መታመሙ ከልጅነቱ ቅንጣት ታህል እንኳ እንዳልቀነሰ እንዲረዳ ከመበረታታት ይልቅ ራሱን እንደ ‘ሁለተኛ ዜጋ’ እንዲያይ ይጋበዛል።

እግዚአብሔርን ግዴታ ውስጥ ስናስገባና በሌላው ደግሞ መኮሰስንና መንፈሳዊ መደቆስን ስንጭን በቃሉም በክርስትናም ላይ ፍትሕ እየተደረገ አይደለም።

## ልምምዳዊነት

የፈውሰኞች ልምምድ ከሰው ወደ ሰው ይለያያል። አንዱ ሌላውን መኮረጁ ደግሞ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ የመጣ ልምምድ መሆኑን ከፈውሰኞች አንድ ዓይነት የፈውስ ሥርዓቶች ይታያል። በአብዛኛው የሚደረገው ግን የፈውስ ፕሮግራም ይባልና በሽተኞች መጥተው ባሉበት ተቀምጠው እያሉ ፈውሰናው “የመገለጥ ስጦታ” በሚባለው በመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ስጦታ ባልተጠቀሰ ነገር ግን በጴንጤው ማህበረሰብ እንደ ጸጋ ስጦታ በሚታይ ልምምድ አማካይነት የሚደረገው የጅምላ “ፈውስ” ነው።

አንዳንዶቹ በሽታን ሁሉ ከአጋንንት እንደመነጨ ያስተምራሉ። ስለዚህ ከሕሙማን ሁሉ ውስጥ አጋንንትን ሊያወጡ ይሞክራሉ። ሌሎቹ ሕመምን ሁሉ ከኃጢአትና ካለማመን ጋር ያቆራኙታል። ሕሙማኑ የሕመሙ ስቃይ ሳያንስ የበደለኝነት ስሜት ሰለባ ይሆናሉ። ሌሎች ሕመምን ሰዎች በራሳቸው አፍራሽ ቃል እንዳመጡት ይናገራሉ። ፈውሱም ገንቢ ቃል መናገር ነው ብለው ያስተምራሉ። ስለዚህ ዘመናቸውን ሁሉ የማይሠራ ቀመር ሲለማመዱ ይስተዋላሉ።

ብዙ ፈውሰኞች በሚያሳዝን መልኩ ተፈወሱ ስለሚሉአቸው ሰዎች የተጋነነና በማስረጃ ያልተደገፈ ምስክርነት ይናገራሉ። ማስረጃ ሲጠየቁ ወደ ኋላ ይላሉ። ፈውስ ሲወሳ ወደጎን መተው የሌለበት ነገር ፈውሱ እውነተኛ መሆኑ ነው። ፈውሱ እውነተኛ እንዲሆን በሽታው እውነት መሆን አለበት። ብዙውን ጊዜ በፈውሰኞች የጅማ ስብሰባዎች የሚደረጉት ፈውሶች የማይረጋገጡ ብቻ ሳይሆኑ በሽታዎቹም ያልተረጋገጡ ናቸው። በሽተኞቹም ያልተረጋገጡ ናቸው። “እዚህ ቦታ እንዲህ በኩል የተቀመጥህ፥ ይህን ነገርህን የሚያምህ ወንድም ጌታ ፈውሶሃል” ዓይነት ፈውስ ነው የሚዥጎደጎደው። የፈውስ ስጦታም ሆነ ፈዋሽ የሆነው ጌታ መለኮታዊ ሥራ ሳይረሳ በዝምታ መታለፍ የሌለበት ዘመናዊው እየተኮረጀ የሚደረግ የፈውስ አገልግሎት ነው። በመጽሐፍ

ቅዱስ ውስጥ “እዚህጋ የተቀመጥሽ እዚህጋሽን የሚያምሽ. . .” የሚባል በጅምላ የሚሰነዘር ፈውስ ኖሮ አያውቅም። ፈውሶች በታዩበትና በተደረጉበት ቦታዎች ሁሉ ፈውሱ እንዲኖር በሽታውና የጌታ ርኅራኄና ፈቃድ ኖረዋል። ለፈውስ የተገቡት ሁለት ዐበይት ነገሮች እነዚህ ናቸው። እምነት ተጠይቆም ሳይጠየቅም ሰዎች ተፈውሰዋል።

በ2008 በታተመ *መጽሐፍ ቅዱስና የአፈታት ስሕተቶች* በተባለ መጽሐፍ ውስጥ የአፈታት ስሕተቶቹ ተግባራዊ ተጋቦት በተወሳበት ምዕራፍ ስለ አንድ ሐሰተኛ የኤድስ ‘ፈውስ’ ዘግቤአለሁ። ፈውሱ እውነተኛ ፈውስ አልነበረም። ኤች አይ ቪ እና ኤድስ በዘመናችን የሕክምና መፍትሔን ያላገኘ ደዌ ነው። በአገራችን ቤተ ክርስቲያን በአንድ በኩል ይህ ቀሳፊ ደዌ እንዳይዛመት ርብርብ ሲደረግ በሌላ በኩል ደግሞ በፈውሰኖች በኩል ጅምላ የኤድስ ፈውስ ሲቸር መስማት እየተለመደ ነው። ይህንን የውሸት ፈውስ ለመግለጥ ያስፈለገው በእውነተኛ ፈዋሽ አምላክ ቤት የሚደረግ ሐሰተኛ የፈውስ ድራማን ለማሳየትና ያልተፈወሱ የኤድስ በሽተኞች በንጹሐን ላይ ሊያደርሱ ከሚችሉት አደጋ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ ለማስረዳት ነው። ይህ የኤድስ ፈውስ እየተደጋገመና ውሸትነቱም እየተረጋገጠ እየመጣ ሲታይ በዝምታ መታለፍ የለበትም።

ከ5ዓመታት የፈውስ ኪዳን መጽሐፍ ደራሲ በሌላ ተአምራት በተሰኘ መጽሐፋቸው በአገልግሎታቸው ካዩአቸውና ከሆኑት ተአምራት መካከል የኤድስ ፈውስም እንደሚገኝ ጽፈዋል። ታዲያ በጊዜው ከላይ የጠቀስኩትን መጽሐፍ በመጻፍ ላይ ነበርኩና በኢሜይልም በደብዳቤም ምስክር የሚሆኑ የተፈወሱ ሰዎችን አድራሻ ጠይቄ ነበር። ያ መጽሐፍ እስኪታተም አላገኘሁም። እስካሁንም አላገኘሁም። በተመሳሳይ ጊዜ በአካባቢዬ በሌላ ፈውሰኛ ከኤድስ ተፈወሱ የተባሉ ሰዎችም ነበሩና ስለነዚያም ከመጋቢው ለማወቅ ሞክሬ ነበር፤ እርሱም ፈቃደኛ አልሆነም። የሰጠኝ ምክንያት፥ “አበሻ ይሉኝታ ስለሚፈራ እንዲታወቅበት አይፈልግም” የሚልና “እምነታቸውን ማጣጣል ይሆናል” የሚል ነበረ። ይህ ሆነ የተባለው ፈውስ እርሱ በሚመግብበት ቤተ ክርስቲያን ስለነበረ እንደ መጋቢ እርሱ ራሱ ማረጋገጫ ማግኘቱን ስጠይቀው አለማግኘቱን ነገረኝ። ይህ ከአገልጋይ የማይጠበቅ ግድ የለሽነትና የሚያስደነግጥ ስንፍና ነው።

## መደምደሚያ ነጥቦች

<u>አንደኛ</u> ፈውስ መኖሩ እውነት ነው። ጌታ ሲያገለግል ፈውሶአል። ፈውስን የአማኞች ብቻ መብት ነው እንዳንል የፈወሰው ደግሞ በእርሱ የተረጋገጠ እምነት የነበራቸውን ሰዎች ብቻ አልነበረም። ደቀ መዛሙርቱን ለአገልግሎት ሲልክም ድውዮችን ሊፈውሱና አጋንንትን ሊያወጡ ነው፤ ማቴ. 10፥8፤ ማር. 3፥15፤ 6፥13፤ 16፥18፤ ሉቃ. 9፥2፤ 10፥9። ከነዚህ ጥቅሶች አንዱን ማር. 16፥18ን ከዐውዱ ጋር ብናየው ይህ ስጦታ ከሚያምኑ ይልቅ ለማያምኑ ምልክት እንዲሆን የተሰጠ መሆኑን ከተልእኮው መረዳት እንችላለን። ተልእኮው፥ *ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ* ሲሆን ምልክቶቹም ወንጌል ለነዚህ ሰዎች ሲሰበክ አጃቢ የሚሆኑ ምልክቶች ናቸው። ወንጌል ሲሰበክ ፈውስ መኖሩ የጌታን ወንጌል ድንቅነትና የወንጌሉን ጌታ ኃይል ገላጭ ነው። ፈውስ በሐዋርያት ዘመንም ነበረ። ፈውስ በዘመናትም ነበረ፤ በዘመናችንም አለ። ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔር ቃሉን የሚያጸናና በሥራ ላይ መሆኑንም ነው።

<u>ሁለተኛ</u> በወደቀች ምድርና በወደቀ ስብእና ውስጥ በመሆናችን በሽታና ሕመም መኖሩም እውነት ነው። በክርስቶስ በጌታችን አምነን ስንድን አዲስ ፍጥረት ሆነናል፤ ሙታን የነበርነው ሕያዋን ሆነናል፤ ጠላቶች የነበርነው ልጆች ሆነናል። የውስጡ ሰዋችን ተለውጦአል። ውጪያዊ ማንነታችን ወይም አካላዊ ሰውነታችን ግል አልተለወጠም። ጌታን ስንቀበል አረጋዊው ወጣት፥ ቀዩ ጥቁር፥ ዕውሩ ዐይናማ አልሆንንም። አካላዊ ሰውነታችን ሊታመም የሚችልና የሚያረጅና የሚሞትም ነው።

ገና አዲስ ክርስቲያን ከነበርኩበት ወራት ጀምሮ ክርስቲያን መታመም እንደሌለበት የሚያስተምሩ ሰዎች ገጥመውኛል። አንሞትም የሚሉ ሰዎችን የሚመራ አንድ ሰውም ሊያሳምነኝ ጥሮ ነበር። አንሞትም የሚሉት መሞታቸው ስለማይቀር ሲሞቱ በአካለ ሕይወት የሉምና መሳታቸውን ለመንገር እድሉ አይኖረንም። አንታመምም የሚሉ ግን ሲታመሙ ችግራቸው ድርብ ይሆናል። በአንድ ወገን ከራሳቸው ጋር ይጣላሉ። ወይ እምነታቸውን መጉደሉን ወይም ኃጢአታቸውን ይፈትሻሉ። ሁለቱም ፍተሻዎች መልካም ቢሆኑም ምክንያቱ እነርሱ ካልሆኑስ? ሌላው ወገን ከእግዚአብሔር ጋር መጣላት ነው። እግዚአብሔር ኪዳኑን ያልጠበቀ፥ ድርሻውን ያልተወጣ አምላክ ይደረጋል። ሁሉን እንደፈቀደ የማድረግ ሉዓላዊነቱ በሰው ሠራሽ ትብታብ ይታሰርና እግዚአብሔር የሰው ፈቃድ አገልጋይ ይሆናል። ይህ ወደ ሦስተኛው ነጥብ ያደርሰናል።

<u>ሦስተኛ</u> ፈውስ ኪዳን ወይም መብትና ሥልጣን ሳይሆን መለኮታዊ በረከት ነው። መብት ይገባኛል የምንለው ነገር ነውና ምስጋናው አይታየንም። ይልቅስ ከጎደለና ካልኖረ የምናጉረመርምበት ነው። በረከት ግን ስንቀበለው የምናመሰግንበት ጸጋ ነው።

<u>አራተኛ</u> እግዚአብሔር በኛ በልጆቹ እርሱ የሚከብርበትን የሚያደርግ ሉዓላዊ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር እርሱ የሚከብርበትንና ልጆቹ በወንድሞች መካከል እንደ በኩራት የሆነውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ ምንም ነገር ወደ ሕይወታቸው የማምጣት አባታዊ ሥልጣን አለው። የሥጋችን ፍቅር ላነሆለለን ክርስቲያኖች የማይገባን ነገር እግዚአብሔር እንዴት ለሥጋ የማይመች ነገርን፥ በተለይም ሕመምን ወደ ልጆቹ ያመጣል? ይህስ እርሱን እንዴት ያስከብረዋል? የሚለው ነገር ነው። ይህ እንዴት እንደሚያስከብረው በሕመም ውስጥ ባለንበት ሁኔታና ጊዜ ላይታየን ይችላል። ደግሞም ከእኛ ውሱን እውቀትና መረዳት የእርሱ ይበልጣል። እንዴት እንደሚከብርም እርሱ ያውቀዋል። ግን የሚቀርጸንን ምንም ነገር የማምጣት አባታዊ ሥልጣን እንዳለው እንወቅ። በዘጸ. 4፥11 ዲዳም ደንቆሮም፥ የሚያይም ዕውርም ያደረገ እርሱ መሆኑን ይናገራል። በዘዳ. 32፥39 እንደሚገድልና እንደሚያድን፥ እንደሚመታና እንደሚፈውስ ይናገራል። ነቢዩ ኤርምያስ በ14፥19 ላይ ስለምን መታኸን ፈውስስ ስለምን የለንም? ይላል። ዳዊት በ41ኛ መዝሙሩ ላይ፥ እግዚአብሔር በደዌው አልጋ ሳለ ይረዳዋል መኝታውን ሁሉ በበሽታው ጊዜ ያነጥፍለታል ይላል። መቀረጽ የሚያሳምም ነገር ነው። ግን ውጤቱ ውብ ነው።

<u>አምስተኛ</u> ሐሰተኛ ፈውሶችና የፈውስ ቀውሶች መኖራቸው እውነት ነው። ሰይጣን የውሸት አባት ነው። ውሸታም ምልክቶችንና ሰይጣን ሠራሽ ተአምራትን የማድረግ ችሎታ አለው። በተለይ በመጨረሻው ዘመን የሚያምኑትን እንኳ እስኪያስት ድረስ ሰይጣን ተአምራትን፥ ምልክቶችንና ሐሰተኞች ድንቆችን ያደርጋል (2ተሰ. 2፥9-10፤ ራእ. 13፥13-15 ወዘተ)። ይህ ሐሰተኛ ፈውስንም ሊነካ አይችልም ማለት አንችልም። በማቴ. 7፥22-23 ጌታ ከቶ አላወቅኋችሁም ያላቸው አስመሳዮች በስሙ ትንቢት የተናገሩ፥ አጋንንት ያወጡና ብዙ ተአምራት ያደረጉ ናቸው።

# ሞርመኖችና የስሑተቶ ትምህርታቸው

በኢትዮጵያ አዲስ ከሆኑ ሃይማኖቶች አንዱ የሞርመኖች ሃይማኖት ነው። በአዲስ አበባ ማኅበሩ ከተጀመረ ጥቂት ቆየት ቢልም (በ80ዎቹ አጋማሽ ነው የተጀመረው) በዝግታ ስሩን በማስፋት ላይ ይገኛል። በ80ዎቹ አጋማሽ በረድኤትና ግብረ ሰናይ አገልግሎቶች ስም የገቡት ሞርመኖች የመጀመሪያ ማኅበራቸው በ1993 ሕጋዊ አካል ኖሮት ሲመዘገብ አሁን 1ሺህ የሚያህሉ አባላት ያሉአቸው 4 ማኅበራት አሉአቸው።

በምኖርበት አካባቢ በርካታ ሞርመኖች አሉ። ጥንድ እየሆኑ ነጭ ሸሚዝና ከራቫት አድርገው ጥቁር ኮትና ሱሪ በቁንጥ ለብሰው ቤት የሚያንኳኩና በመንገድ ሰዎችን እያገኙ በማነጋገር ሃይማኖታቸውን የሚሰብኩ በርካታ ወጣት መልእክተኞች በአካባቢያችን ይታያሉ። አንድ ቀን ሁለቱ ወደ ቤቴ ስገባ ሰላም አሉኝና ቆመን ማውራት ጀመርን። ስለ እግዚአብሔር ማንነት ስናወራ፥ "እውነት እግዚአብሔር እንደኛ ኃጢአተኛ ሰው የነበረና አሁን የሆነውን የሆነ አምላክ ነው?" አልኳቸው። ለጊዜው ጥያቄውን ሊያለሰልሱ ቢሞክሩም በግልጽ አልመለሱልኝም።

ስለ ክርስቶስ እንድናወራ ፈልጌ፥ "እውነት ክርስቶስ ደግሞስ የሰይጣን መንፈሳዊ ወንድም ነው ብለህ ታምናለህ?" አልኩት አንደኛውን። እናውቃለን ይበሉ እንጂ እውነተኛውን ጌታ የማያውቁ ሰዎች ስለሆኑ አጋጣሚውን በመጠቀም ስለ ጌታና ስለ መስቀሉ ሥራ ነገርኳቸው።

መጽሐፋቸውን ጨርሼ አላነበብኩትም ከውስጡ ግን ጥቂት ቦታዎችን ይዤ ስለነበር ከመለያየታችን በፊት፥ "አንድ የመጨረሻ ጥያቄ ልጠይቃችሁ" አልኳቸው። እነርሱ ነጮች እኔ ጥቁር ነኝና፥ "ጥቁር የሆንኩት ወይም ጥቁር ቀለም የኖረኝ ተረግሜ ይመስልሃል? ይህንን ታምናለህ?" አልኩት ከሁለቱ አንዱን። እርሱም እንደማያምን ነገረኝ። እስኪ የሞርመን መጽሐፍ የሚባለውን መጽሐፍህን አውጣና በ2ኛ ኒፋይ ምዕራፍ 5 የተጻፈውን እንይ አልኩት። ክርስቲያኖችን ለመሳብ ሲሉ ይህንን መጽሐፍ አንዳንድ ጊዜ አይይዙትምና ያን ቀን አልያዘም። ደግሞም ያንን ቃል ፈጽሞ እንዳላነበበና እንዲያውም እንዳልተጻፈ ነው ተከራከረኝ። ገና መጽሐፋቸውንም ያላወቁ ወጣቶች መሆናቸውን አስተውዬ በሌላ ጊዜ እንገናኝ ተባብለን ቀጠሮ ሰጠኋቸው፤ ግን አልመጡም፤ አልተገናኘንም። በዚያ ክፍል ኒፋይ የተባለው ሰው ነጮችና መልከ መልካም የነበሩ ሰዎች ባለመታዘዛቸው ቆዳቸው የጠቆረና መልካቸውም አስቀያሚ እንዲሆኑ የተረገሙ መሆናቸውን ይናገራል። ተረግመው ጥቁር ከሆኑ በአገራችንም ሆነ በሌላው አገር ያሉት ሞርመኖች ሞርመን ሲሆኑ ወደ ነጭነት መመለስ አለባቸው ማለት ነው።

የጥቁሮች መጥቆር የመጽሐፋቸው ትልቁ ስሕተት አይደለም። ሳነብበው ስላስገረመኝ ነው ያንን ክፍል በቃል የያዝኩት እንጂ መጽሐፋቸውን አንብቤ አልጨረስኩትም እያነበብኩት ግን ነኝ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አግጥጦ የሚጣላ መጽሐፍና ትምህርት ነው ያላቸው። ከስሕተት ትምህርቶቻቸው ጥቂቶቹን በዚህ ክፍል ሳሰፍር አንባቢዎች ይህንን ሃይማኖት በጥቂቱም ቢሆን ምንነቱን እንዲያስተውሉ ለማድረግ ነው።

የሞርመኖች ሃይማኖት መሠረቱ ስሕተት ስለሆነ መሠረቱ ከተበላሸ ጠቅላላው መዋቅርና በመሠረቱ ላይ የተገነባው በሙሉ ትክክል አይደለም ማለት ነው። መሠረታዊ የአስተምህሮ ስሕተቶቻቸውን ገረፍ ገረፍ በማድረግ መመልከት መልካቸውን ሊያሳየንና ተጠንቅቀን እንድናስጠነቅቅ ሊረዳን ይችላል። በዚህች መጣጥፍ በጥቂት መሠረታዊ የተሳሳቱ ትምህርቶቻቸው ብቻ ላይ ላተኩር እወዳለሁ።

## መጽሐፍ ቅዱስ ሲደመር ምን?

ከመጽሐፍ ቅዱስ መነሣቱ ከሥልጣን ምንጫችን እንድንንደረደር ያደርገናል። ሞርመኖች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እኩያ ሥልጣን አላቸው ብለው የሚያምኑአቸው ሌሎች መጻሕፍት አሉአቸው። እነዚህም The Book of Mormon (የሞርመን መጽሐፍ) እና The Pearl of Great Price (የከበረው ዕንቁ) እንዲሁም Doctrines and Covenants (ትምህርቶችና ኪዳናት) የሚባሉት መጽሐፎቻቸው ናቸው።

በተለይ የሞርመን መጽሐፍ የሚባለው ምንጩ አጠያያቂ ነው። በርካታ የምካቴ እምነት (Apologetics) ጸሐፊዎች እንደሚያምኑት ሰሎሞን እስፖልዲንግ የተባለ ሰው የጻፈው ያልታተመ ልብወለድ ሲድኒ ሪግደን በሚባል ሰው አማካይነት በጆዜፍ እስሚዝ እጅ ገብቶ የሞርመን መጽሐፍ ተሰኝቶ ተጻፈ ይላሉ። የሃይማኖቱ ጀማሪ ጆዜፍ እስሚዝ የሚለው እና በሃይማኖቱ የሚነገረው ጆዜፍ ኒው ዮርክ አጠገብ ከሚገኝ መኖሪያ ቤቱ አጠገብ ከሚገኝ ኮረብታ በጥንት የግብጽ (Reformed Egyptian) ፊደሎች ከተጻፈ የወርቅ ቅጠሎች መጽሐፍ ኡሪምና ቱሪም ባለው ምትሃታዊ መነጽር እያተመለከተ የተረጎመው መሆኑ ነው። Reformed Egyptian የሚባል ቋንቋና ጽሑፍ አለመኖሩን የራሳቸው አርኪዮሎጂስቶችም ጭምር የሚመሰክሩ ሲሆን በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱት በአሜሪካ የሚገኙ ስልጣኔዎችና ሕንፃዎች በታሪክም በቁፋሮም ያልተገኙና ሊገኙ የማይችሉ ናቸው። ለቁጥር የሚበዙ ከገሃዱ ታሪክ ጋር የሚጋጩና ምንም ማስረጃ ሊቀርብላቸው የማይቻልባቸው ትረካዎች ያሉበት ሥራ ነው። ይህ የወርቅ ቅጠሎች መጽሐፍ ደግሞ ትርጉሙ ካለቀ በኋላ የሚባለው አስቀድሞ የተደበቀበትን ቦታ ያሳየው ሞሮኒ የተባለው መልአክ መልሶ ወደ ሰማይ ይዞት ሄደ ይባላል። ስለዚህ ምንም ማስረጃ የማይገኝለት በመሆኑ ማስረጃ መፈለግንም አላስፈላጊ ያደረገ ክስተት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቃሉ ስለራሱ የሚነግረን ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የተናገሩት / የጻፉት እንጂ በሰው ፈቃድ ያልመጣ መሆኑን ነው። ከዚህ ቃል መቀነስ እንዲሁም በዚህ ቃል ላይ መጨመር እንደሌለብን ቃሉ ያስጠነቅቀናል። ሞርመኖች የሚያደርጉት ከቃሉ ጋር እኩያ ሥልጣን ያላቸው መጻሕፍት መጨመር ነው። ቃሉ ተጨማሪ አዲስ መገለጥ የማያሻው ሙሉ ነው።

# እግዚአብሔር ሰው ወይስ ምን?

ስለ እግዚአብሔር ያላቸው ነገረ መለኮት ከሁሉም የከፋና የስሕተታቸው መሠረት ነው። እግዚአብሔር በሌላ ዓለም ውስጥ ሰው ሆኖ ይኖር የነበረና በኋላ ከብሮ አምላክ የሆነና በዚህች እኛ በምንኖርባት ዓለም አምላክ የሆነ ነው ብለው ያስተምራሉ። ይህ አምላክ ወደዚህች ዓለም ተመድቦ ሲመጣ አምላክ ከሆነች ሚስቱ ጋር አብሮ መጣ። የከበረውም ቀድሞ ሰው በነበረበት ዓለም የነበረውን አምላክ በፍጹም በመታዘዙ ነው።

እግዚአብሔርን የላከው አምላክ የከበረው ደግሞ ሌላኛውን አምላክ በመታዘዙ፤ ያም በተራው ሌላኛውን በመታዘዙ እያለ ይቀጥልና የአምላክ ቁጥር መጨረሻ የሌለው ይሆናል። ስለዚህ በሞርመን ትምህርት አንድ እግዚአብሔር የለም የለም ማለት ነው።

የዚህ ትምህርታቸው ሌላው ገጽታ እግዚአብሔር ቀድሞ እንደኛ የመሰለ ሰው ከነበረና አሁን አምላክ ከሆነ ሰውም አንድ ቀን ከብሮ እንደ እግዚአብሔር ይሆናል ማለት ነው። ይህም በግልጽ የተቀመጠ ትምህርታቸው ነው። መንፈስ ሳይሆን የሥጋ አካልና አጥንት ያለው ይህ አምላክ እና ሚስቱ በሰማይ የመንፈስ ልጆችን እየወለዱ እነዚህ የመንፈስ ልጆች ደግሞ መጥተው በምድር የሚኖሩ ሰዎች አካል ሆነው ይወለዳሉ።

ሞርመኖች ትምህርተ ሥላሴን አይቀበሉም። ወይም በሦስት አካላት የተገለጠ አንድ አምላክ መሆኑን አይቀበሉም። መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው የመንፈስ አካል ነው ይላሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የሚነግረን አንድና ያልተፈጠረ የሁሉ ፈጣሪ የሆነ አምላክ መሆኑን፥ የማይለወጥና ዘላለማዊ መሆኑን፥ ሥጋና አጥንት ያለው አካል ሳይሆን መንፈስ መሆኑን ነው። እግዚአብሔር ሥላሴ መሆኑ በቃሉ በግልጽ የተጻፈ ነው።

# ክርስቶስ የሰይጣን ወንድም?

የሞርመኖች ሙሉ ስያሜአቸው የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ወይም The Church of Jesus Christ od Latter-day Saints በምሕፃረ ቃል LDS ተብለው ነው። በይፋ መጠሪያቸው የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ቢኖርበትም ቀርበው ሲታዩ ግን የእነርሱ ክርስቶስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሳይሆን ሌላ ኢየሱስ ሆኖ እናገኘዋለን። ሌላ ኢየሱስ መሰበክ የጀመረው ገና ከነጳውሎስ ዘመን እንደነበረ ከ2ቆሮ. 11፥4 እናገኛለን። በመንገድ ላይ ወይም በቤት አግኝተን የምናነጋግራቸው ሞርመኖች እኛ ምናመልከውን ክርስቶስ እንደሚያመልኩ አስረግጠው ሊያሳምኑ ይሞክራሉ። ይህን ሲያደርጉ ወይም ራሳቸውም የሚያመልኩትን አልተረዱትም፤ ተረድተው ከሆነ ደግሞ እየሸነገሉን ነው።

በ2008 ያረፈውና ከ1995 ጀምሮ እስኪሞት ድረስ የሞርመኖች ቤተ ክርስቲያን መሪና ነቢይ የነበረው ሰው በ1998 በተጻፈ የቤተ ክርስቲያናቸው ዜና የተናገረው ሞርመኖች የሚያምኑት ክርስቶስ ክርስቲያኖች ከሚያምኑት ክርስቶስ የተለየ መሆኑን ያሳየ መግለጫ ነበር። ያለው እንዲህ ነበር፥ "እኔ ስለ እርሱ የምናገረው ክርስቶስ በተለምዶ የሚነገርለት ክርስቶስ ሳይሆን በዚህ በመጨረሻው ዘመን የተገለጠው ክርስቶስ ነው። እርሱም ከአባቱ ጋር ለወጣቱ ጆዜፍ እስሚዝ በ1820 የተገለጠው ነው። እርሱ [ጆዜፍ] በዚያ ቀን ከዚያ ጥሻ ሲወጣ በዓለም ላይ በየትኛውም ዘመን ከኖሩት የወንጌል አገልጋዮች ሁሉ የላቀ የመለኮትን ባህርይ እውቀትን ተሞልቶ ነበር።"[1]

ይህ ጥቅስ በመሪው አንደበት የተነገረው ግልጽ ሌላ ክርስቶስ እንደሆነ ይመሰክራል እንጂ ሞርመኖች ክርስቶስ የሚሉት በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለጠልን፥ በመስቀል ቤዛ ሆኖልን የሞተልን አምላክ ከቶም አይደለም። የሞርመኖች ክርስቶስ ፍጡር ነው። በሞርመኖች ኃይማኖት ኢየሱስ የአንድ አምላክና ሴት አምላክ የሆነች ሚስቱ ፍሬ ሲሆን የሰይጣን የመንፈስ ወንድም ነው። የእኛም የመንፈስ ወንድም ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚያስተምረን ክርስቶስ የሥላሴ ሁለተኛ አካል፥ ከጥንት ዘላለማዊና ፈጣሪ የሆነ፥ ቤዛችን ሊሆንና ኃጢአታችንን በመስቀል ሊሸከም ሥጋ የለበሰ መሆኑን ነው።

# ቤተ ክርስቲያን

ጆዜፍ እስሚዝ በ The Pearl of Great Price መጽሐፉ ሌሎች ቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ ሙሉ በሙሉ የተበላሹና በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊዎች እንደሆኑ ጽፎአል። ይህ አዳዲስ ሃይማኖቶች ሲጀመሩ ራሳቸውን ብቻኛዋና ንጹህዋ የእዚአብሔር መሣሪያ አድርገው የሚያቀርቡበት ስልት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ግን በየትም ቦታና በየትኛውም ዘመን ያሉ አማኞች ሁሉ እውነተኛዋ የክርስቶስ አካል የተሠራችባቸው ሕያዋን ድንጋዮች እንደሆኑ ነው።

# ሌሎች ልምዶች

ድነት (ደኅንነት) በጸጋ ሳይሆን በማመንና በሥራ ነው ብለው ይቀበላሉ። የመዳን ቁንጮው ደግሞ አምላክ መሆንና ያ አምላክ የሆነ ሰው የግል ዓለም ኖሮት እነዚያን ሰዎች መግዛት ነው።

ብዝሐ ጋብቻ 9ብዙ ሚስቶችን ማግባት) የሞርመኖች የተለመደ ባህል ነው። ይህ ሃይማኖቱ ከተጀመረበት ከአሜሪካ መንግሥት ጋር ያጋጨ ተግባር ሲሆን አሁን ተግባሩ እንደሌለ በቃል ቢነገርም በተግባር ግን አይደለም። እንዲያውም ይህን እንዳይቀር የሚፈልጉት ቡድኖች ተለይተው የራሳቸውን ማኅበር እየመሠረቱ ወጥተዋል።

ሕያዋን አማኞችን ብቻ ሳይሆን ሙታንን ማጥመቅና ለሙታን መጠመቅ የሞርመኖች ልማድ ነው። አንዲት ሴት ለብዙ ሺህ ሰዎች ከመጠመቋ የተነሣ አንድ የቤተ ክርስቲያኗ ሰው ስለ እርሷ ሲናገር ከኢየሱስ የበለጠ ብዙ ሰዎች አድናለች ሲል አድንቆአታል።

እነዚህ ጥቂቶች የሞርመኖች እምነትና ተግባራት ገላጭ ነጥቦች ናቸው። ይህ ሃይማኖት እያደገ ብቻ ሳይሆን በፍጥነት እያደጉ ካሉ ሃይማኖቶች አንዱ ነው። ለጥቁሮች ገጽ ንቀትን የሚያሳይ ሆኖ በጥቁሮች መካከልም እያደገ መሆኑ በሚቀበሉት ዘንድ ምንነቱ ያልተስተዋለ መሆኑንም ያሳያል። አገልጋዮች ስለዚህ ሃይማኖት ቢያንስ መጠነኛ እውቀትና ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል እላለሁ።

[1] LDS Church News, June 20, 1998, p. 7

# ንገረው

አትፍራው ንገረው
ንገረው አትፍራው
ክፉ እንደሆን ሥራው
ማመሰቃቀሉን ቀኙን ወደ ግራው
የአምላኩን ኪዳን
እርግፍ አርጎ ትቶ
ከፍሊጋው ርቆ
ከመንገዱ ስቶ
ሰውን እያሳተ መሆኑን ንገረው
ፀሐይዋ ጠልቃበት መከራ ሳይመክረው



ጠል መከልከሉ፥
ሰማይ መዘጋቱ፥
ውኃው መመጠጡ፥
ምድር መገርጣቱ፥
አትፍራው ንገረው
እርሱ እንደሁ ምክንያቱ፤

አትፍራት ንገራት
ምክንያቱ እርሷም ናት
ያገሯን አማልክት
የወንዟን አጋንንት
ይህች ክፉ አታላይ
ጭና በጀርባው ላይ
ባሏን እንደ ጌኛ ለጉማ የነዳችው
የጌታን ነቢያት አሳዳ የፈጀችው
እርሷ ናት
ንገራት።

እጥፍ ድርብ ሆኖ
ዋጋ ተተምኖ
ትከፍያለሽ በላት።